አፍሪካ ቲቪ

8

# አፍሪካ አካዳሚ

# AFRICA ACADEMY

ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት

# የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

በቴሌግራም

4

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# ሱራቱ አል-አስር

(የጊዚያት ምዕራፍ) በመካ የወረደ ምእራፍ ነው፡፡ የአናቅፁ ብዛት ሶስት ናቸው፡፡

ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-

የትርፋማነትንና የከስረትን እውነታ እና የሰው ልጅ የሚኖርበት ጊዜን አስፈላጊነት የሚያብራራ ምዕራፍ ነው።

8

አፍሪካ አካዳሚ

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

(1) በጊዜ እምላለሁ፤ (አላህ በዐስር ወቅት ይምላል።)

(2) የሰው ልጅ በሙሉ በእርግጥ በክስረት እና በጥፋት ውስጥ ናቸው።

(3) ነገር ግን እነዚያ በአላህ እና በመልዕክተኞች በትክክል ያመኑትና መልካም ሥራን የሰሩ፤ እርስ በርሳቸው በእውነት እና በትዕግስት ላይ የተመካከሩ እና አደራ የተባባሉ፤ እንዲሁም በመታገስም አደራ የተባባሉ ብቻ ሲቀሩ፡፡ (በእነዚህ ባህሪያት የተገለፁ ሰዎች ከክስረትና ከጥፋት የሚድኑ ናቸው።)

8

## ይህ ምዕራፉ የሚያስተምራቸውን አራት ዋና ዋና ነገሮችን መፈፀም ግድ ነው፡፡

- 1ኛ. እውቀት ሲሆን፡- እሱም አላህን፤ መልዕክተኛውን እና ኢስላምን ማወቅ ነው፡፡ ምክንያቱም አላህን ያለ እውቀት መገዛት ፋይዳ የለውም፡፡ ይህን ያደረገ ሰው የጠመመ ሲሆን በዚህም ተግባር ስህተት ላይ ይወድቃል፡፡
- 2ኛ. ተግባር ሲሆን፡- አውቆ በእውቀቱ ያልሰራበት ሁሉ በእውቀታቸው ያልሰሩትን አይሁዶች ይመስላል፡፡ ከሰይጣን ዘዴዎች አንዱ ሰዎችን ካወቁ እንደሚጠየቁና ካላወቁ ግን ከዚህ ችግር ነፃ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማስመሰል ከትምህርት መድረክ ማሸሽ ነው፡፡
- 3ኛ. ወደዚሁ ዲን ጥሪ ማድረግ ሲሆን፡- አዋቂዎችና ዳዒዎች የነቢያት ወራሾች ናቸው፡፡ አላህ የኢስራዒል ልጆችን (ይሰሩት ከነበረው መጥፎ ተግባር አይከላከሉም ነበር) እንዳላቸው ስለ ነበሩ ረገማቸው፡፡ ደዕዋ ማድረግና ማስተማር ሁሉም ከተወው ሁሉንም ወንጀለኛ የሚያደርግ እናም በከፊል ህብረተሰብ እንኳን ቢሆን ሊሸፈን ግዴታ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡
- 4ኛ. በማስተማር፤ በመተግበርና ወደ እሱ ጥሪ በማድረግ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ አያሌ መሰናክሎችን ለማለፍ ትዕግስት ማድረግ ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ትዕግስት ለሁሉም ነገር አስፈላጊ ነው፡፡
- በተለይም ለመልካም ሰሪዎች እንዲሁም በይበልጥ ሰዎችን ለማስተማር ለሚያስቡ ሁሉ ለስራቸው መቃናት ከሁሉ የበለጠ አስፈላጊው ነገር ትዕግስት ነው፡፡
- ሉቅማን ለልጃቸው ከለገሰሱለት ምክር መካከል የሚከተለው አባባል ነበረበት ‹‹ልጄ ሆይ! ሶላትን አስተካለህ ስገድ በበጎ ነገርም... በሚያገኝህ መከራ ላይ ታገስ››

# ከሱረቱል አሥር ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- 1. ከሃዲ መጨረሻው ዘልአለማዊ ክስረት መሆኑን፤
- 2. በአላህ ያመኑና መልካም የሰሩ ሰዎች ክብርና ግዴታ መሆኑን፤
- 3. በኢማን፣ በመልካም ሥራ፣ በእውነትና በትዕግስት የመመካከርን ባህሪ ያልተላበሱ ሰዎች ከሳሪዎች መሆናቸውን።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com